# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 322 ሐምሌ 4 2006

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

## ፋሽስታዊ ፕሮፖጋንዳው እና ምላሻችን!

**የግንቦት 7 መግለጫ**

**ሐምሌ 3 ቀን 2006 ዓ.ም.**

ዘረኛውና ፋሽስታዊ ወያኔ፣ የኢትዮጵያዊያንን የትግል መንፈስ ለመስበር እና <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነትና ለፍትህ የሚያደርገውን ትግል ወኔ ለመስለብ ያቀደበትን</u> የመጀመሪያውን ፕሮፖጋንዳ ለቀቀ። የህግ ልጓም የማያውቀው ፋሽስት በግፍ የያዛቸውን ሰዎችን እይስሙላው ፍርድ ቤት እንኳን ከመቅረባቸው በፊት "ወንጀለኛ" እያለ እንዲህ ዓይነቱ ፕሮፖጋንዳ እንደሚነዛባቸው ተደጋግሞ የታየ በመሆኑ ይህ ፕሮፖጋንዳ የሚጠበቅ ነበር። ሆኖም ግን ፕሮፖጋንዳው ያዘጋጁ ሰዎች ተስፋ ያደረጉትን ውጤት ያመጣ አልሆነም። ወደፊት ደግሞ ሌሎች ሙከራዎች ይደረጉ ይሆናል፤ ውጤታቸው ግን ከዚህኛው የተለየ እንደማይሆን ይገመታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኢቲቪ የእውነት ጥፍጣፊ እንኳን እንደማይገኝ ያውቃል።

በአሁኑ ተቆራርጦ በተለጣጠፈ ፊልም በታጀበው ፕሮፖጋንዳ ውስጥ፣ መሪያችን አንዳርጋቸው ጽጌ በምግብና ውሀ እጦት ብቻ ሳይሆን በተፈጸመበት የተለያዩ የማሰቃያ ወንጀሎች ብዛት አካሉ መዳከሙ ይታያል። ያም ሆኖ ግን ከእሱ ወጥተው እንድንሰማቸው የተደረጉት ቃላት የመንፈሱን ጥንካሬ ገላጮች ናቸው። እሱ ሥራውን መጨረሱንና በዚህም ምክንያት ህሊናው የተረጋጋ መሆኑን ነው የሰማናቸው ቃላት የነገሩን። በዚህ አጭር አጋጣሚ እሱ ግዴታውን ማጠናቀቁ፤ ሀገራችን ከወያኔ ፋስሽቶች ነፃ የማውጣት ኃላፊነቱ በእኛ ትከሻ ላይ መውደቁን ነገረን። ለዜናው ማጀቢያነት የገቡት ፎቶግራፎችም መሪያችን ፈታኝ በሆነ የተፈጥሮ አካባቢ የከፈለውን መስዋዕትነት የሚመሰክሩ ሆነው ተገኙ።

ጀግናው አንዳርጋቸው ጽጌን በተጎሳቆለ ሁኔታ ማየት ስሜትን የሚጎዳ ቢሆንም የመጀመሪያው ስሜት ካለፈ በኋላ ከፊልሙ በአዕምሮዓችን የሚቀረው ከላይ በአጭሩ የተገለፁት ጥንካሬውና ኃላፊነትን ወደ እኛ በይፋ ያስተላለፈበት አጋጣሚ መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ የተሠራው የመጀመሪያ በምስል የተደገፈ የወያኔ ፕሮፖጋንዳ ከታለበት ዓላማ በተፃራሪ የወያኔን ሹማምንት አውሬነትና የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ትልቅነት አሳይቷል።

ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለፀው ይህ የመጀመሪያ የፕሮፖጋንዳ ሥራ እንጂ የመጨረሻው አይደለም። የማስተዋል ችሎታ ያነሳቸው የወያኔ ፕሮፖጋንዲስቶችም ፊልማቸው ቁጣን ማባባሱ ሲያዩ ፈጥነውም ይሁን ዘግይተው ከዚህ በተለየ አቀራረብ መመለሳቸው አይቀርም። ስለሆነም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ የጅል ፕሮፖጋንዳ መንፈሱን እንዲጠብቅ ማሳሰብ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። የወያኔ ፕሮፖጋንዲስቶች አሁን የደረሰባቸውን ኪሳራ ለማካካስ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ያላለውን አለ ይሉን ይሆናል፤ ቃላትን ፈጥረው እሱ የተናገራቸው ያስመስሉም ይሆናል። የቻይና ቴክኖሎጂ ከወያኔ ድድብና ጋር ሲደባለቅ ምን እንደሚያመጣ አስቀድሞ መገመት ያዳግታል። ኢቲቪ ለዘመናት የተካነበትን ውሸት የመፈብረክ ክህሎትን ወደ ላቀ ደረጃ የማሳደግያ አጋጣሚ አድርጎ ሊጠቀምበት ስለሚችል መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ ተገቢ ነው።

ከዚህ በተረፈ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጥብቅ ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ አለ።

ጀግናው፣ ብልሁና አስታራቂው አንዳርጋቸው ጽጌ ኢትዮጵያን በማጥፋት ዓላማ ባበሩ፤ ዘርፈውና በልተው በማይጠግቡ፤ የንፁሃንን ደም መጠጣት በለመዱ ዘረኞችና ፋሽስቶች መዳፍ ውስጥ ነው። ለዚህ ምላሻችን ምንድነው? ገና ከአሁኑ እንደታየው በሰላማዊ መንገድ ሥርዓቱን ለመገዳደር የደፈሩ ወጣቶችን ለማሰር አንዳርጋቸው ጽጌን ሰበብ ሲያደርግ የኛ ምላሽ ምንድነው? አገራችን ያፈራቻቸው ምርጥ ዜጎች በሙሉ ወይ ታስረው አልያም ተሰደው ሲያልቁ እያየን ምን እየሠራን ነው? ነፃነታችንና አገራችን ለህወሓት ዘረኞች አስረክበን እንቀመጣለን?

በጭራሽ!

አንዳርጋቸው ጽጌ የተመቻቸ ኑሮዉንና ልጆቹን ጥሎ ለነፃነቱና ለሀገሩ የዘመተ ጀግና ነው። <u>ከእኛም የሚፈለገው ይህንኑ ነው</u>። ጀግናችንን ብቻ ሳይሆን አገራችንም ጭምር ከታሰረችበት ማስፈታት የምንችለው ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ግዜ

## አዋጅ አዋጅ !!!……….. ልብ ያለዉ ልብ ይበል ጆሮ ያለዉ ይስማ !!

**የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል የተሰጠ መግለጫ**

**አዋጅ አዋጅ !!!**

ልብ ያለህ ልብ በል ጆሮ ያለህ ስማ !!

የግንቦት7 ህዝባዊ ሃይል የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በየመን መታገት አስመልክቶ አጭር መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል።በመግለጫችን የመን ታጋዩን ልታግት የምትችልበት የጸጉር ስንጣቂ የምታክል ምክንያት እንደሌላት ሊኖራትም እንደማይችል ስለሆነም ታጋዩ ባስቸኳይ እንዲለቀቅ በተደጋጋሚ ጠይቀን፣ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የነጻነት ታጋዩ ለፋሽስቱ የወያኔ ቡድን ተላልፎ ቢሰጥ የመን የማይሰረዝ ታሪካዊ ስህተት የምትሰራ መሆኑን ህዝባዊ ሃይላችንም የበቀል እርምጃዎችን እንደሚወስድ አሳውቀን ወያኔም ምናልባት ትግሉን አስቆማለሁ በሚል የሞኝ ስሌት ያደረገው ከሆነ ድርጊቱ ትግሉን በዕልህ እና በበቀል አጅቦ ከመውሰድ እና ከማፋጠን የዘለለ ትልቁ የሃሳብ አባት አንዳርጋቸው በሃገሪቱ ሰማይ ላይ የለቀቀውን የኢትዮጵያዊነት ጻረ ወያኔ መንፈስ አስሮ አሰቃይቶ፣ገሎ ማስቆም እንደማይችል አሳስበን አስገንዝበን ነበር። መግለጫችን የተጻፈበት ቀለም ሳይደርቅ ግን የየመን መንግስት እንደሰጋነው ትልቁን የቁርጥ ቀን ልጅ ለወያኔ አሳልፎ መስጠቱን አውቀናል።

የተከበርከው የታላቅ ታሪክ ባለቤት የሆንከው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ አሁንስ ምን ትጠብቃለህ?? ምንቀረህ ?? ያለህበትን ሁኔታ የሚገልጽ ከዚህ በላይ ገላጭ ነገር ከቶ ከወዴት ይመጣል??ወያኔ የአንዳርጋቸው በእጁ መግባት ለጊዜውም ቢሆን ከሚፈጥርለት ፌሽታ ጎን ለጎን እገታው በይፋ ከተገለጸበት ቅጽበት ጀምሮ ግን የሚፈራው የሚጠላው ነገር ብቅ ብሏል፡- የአንድነት መንፈስ!! የጋራ ድምጽ!! እገታው ለኢትዮጵያ ህዝብ በይፋ ከተነገረ በኋላ በሁሉም አቅጣጫ የሚኖር መላው ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ አመለካከት እና ፍልስፍና ሳያግደው ለአንዳርጋቸው ያለውን ድጋፍ እና ያገባኛል ባይነቱን አሳይቷል፣እያሳየ ነው፤ገልጿል እየገለጸ ነው።

ይህ መጥፎ አጋጣሚ ለተቃውሞ የፖለቲካ ትግሉ ይዞት የመጣው መልካም ሁኔታ እና ክስተት ይኸው ነው፤ ተባብሮ መጮህ!! የተባበረ ነጎድጓዳዊ ቁጣ!!

በእውኑ ከዚህ በላይ ወያኔን የሚያሸብር ዙፋኑን የሚያርድ ጉዳይ ከወዴት ይገኛል?? የትም።

የተከበርከው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ከቶ በምን አይነት አመክንዮ እና የታሪክ ምጸት ነው ወያኔን የመሰለ አንድ ተንቀሳቃሽ የሽፍታ ቡድን ተሰደን እንኳን መተንፈስ እንዳንችል አድርጎ ለ 23 ዓመታት ቀጥቅጦ እና አዋርዶ ሊገዛን የቻለው??

እራሳችን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ከፍለን የተባበረ ክንዳችን የጋራ ጠላታችን ላይ ማንሳት ባለመቻላችን አይደለምን?? ነው እንጅ!!!

የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል በዚህ ታሪካዊ ወቅት የታሪክ ጠርዝ ላይ ቆሞ የሚያስተላልፈው መልዕክት አለው፡-

እስከመቸ ነው ጥቁሩን በሬ ጅብ ሲበላው ነጩ በሬ ሳይደንቀው፣ያጣማጁ ደም ሳይሸተው፣ ነጩን በሬ ጅብ ሲከበው ጥቁሩ በሬ አደጋውን የነጩ ብቻ አድርጎት ጉዳዩን ችላ ሲለው በመጨረሻ ግን ሁለቱም የጅብ መንጋ ሲሳዮች ሲሆኑ ተረት እየተተረተብን የምንኗዘው???? ሃገራችን ጨርሳ እስክትጠፋ ማህበረሰባችን እስኪበተን ነውን?? ብዞዎቻችን የምናውቀውን አንድ ታሪክ እዚህ ላይ ብንጠቅስ ያለንበትን ሁኔታ በተወሰነም ደረጃ ቢሆን ለማሳየት የሚረዳ ይመስለናል።ናዚ ወደ ስልጣን ሲመጣ እና የስልጣን ማማ ላይ ቆሞ የሚሰራውን እየሰራ በነበረበት ወቅት ላይ የወቅቱ የጀርመን ልሂቃን ዝምታ የገረመው አንድ አስተዋይ ታላቅ ሰው ይህን ታዝቦ ነበር፡- ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ አንዳርጋቸውን ያፈነበትን እለት የሚረግምበት ቀን ሩቅ አይደለም!

የህወሃት ጉጅሌ እንደማንኛውም አምባገነን ከፊት ከነበሩ አምባገነኖች ቅንጣት ትምህርት አልተማረም። ወያኔዎች በእብሪት የያዙት ስልጣንና ከህዝብ የዘረፉትን ንብረት የሚያጡት እየመሰላቸው በባነኑ ቁጥር የነጻነት አርበኞችን በማፈን በመግደልና በማሰቃየት ፍርሃታቸው የተወገደ ይመስላቸዋል።

ወያኔ የእኛ መሪና የኢትዮጵያ ህዝብ የነጻነት አርበኛ በሆነው አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ ያካሄደው አፈና ከአፈናውም በሆላ በሚያደርሱበት አካላዊ ስቃይ ፍርሃታቸው የሚወገድ ወይም ስርአታቸው ከሞት የሚተርፍ መስሏቸው ከሆነ በእጅጉ ተሳስተዋል። አንዳርጋቸው ዛሬ በእጃቸው ሆኖ በነጻነት ይኖር ከነበረበት በበለጠ የሚለበልባቸው የውስጥ እግር እሳት ይሆናል።

አንዳርጋቸው ሰበአዊ ምቾቱንና ለራሱና ለቤተሰቡ መኖርን አቁሞ የኢትዮጵያን ህዝብ ነጻነት በህይወቱ ሊጋፈጥ ከቆረጠ ቆይቷል። እኛ የትግል ጓዶቹና ለህዝብ ነጻነት የቆሙ ሃይሎች ሁሉ አንዳርጋቸውን እናውቀዋለን። ወያኔ በአካሉ ላይ የለመደውን ስቃይ ጀምሮበታል፣ ከዚህ የበለጠም ጉዳት እንደሚያደርስበትም እናውቃለን። የአንዳርጋቸውን ታላቅ የነጻነት ሰውነትና ክብረ ህሊናውን፣ በአርበኝነቱ የሚሰማውን የኩራት ስሜቱን ለግፈኞች ያለውን ንቀትና መጸየፍ ሊለውጡ እንደማይችሉ አስረግጠን እናውቃለን።

አንዳርጋቸው እንደሁላችን ሰው ነውና በፈሪዎች በትር የሚደርስበት አካላዊ ስቃይ ግን ለህዝባችን የገባነውን ቃል ውሳኔያችንን እና አቋማችንን እንደብረት ያጠነክረዋል እንጂ አያላላውም።ይልቁንም በአንዳርጋቸው መታፈን ምክንያት ከመላ ሀገራችን በአለም ዙሪያ ከተበተነው ኢትዮጵያውያን እና ሌሎች የነሰታነት ሃይሎች የምንሰማውና እየሰማን ያለነው የሚያስገመግም ህብረ ድምጽ ከብረት የሚያጠነክር ሃይል ሆኖኗል።

አንዳርጋቸው የዘራው የነጻነት የአርበኝነት ዘር ከመብቀል አልፎ እየጎመራ በመሄድ ላይ ነው። አንዳርጋቸው ሺ አንዳርጋቸውን ተክቷል። ወያኔ አንዳርጋቸውን በማፈንና በእጁ አስገብቶ በራሱ መስኮት ቲቪ ስቃዩን እንግልቱን በማሳየት ሊያላምጠው የማይችል የብረት እንክብል ነው የነከሰው። ይህንንም ሳይውል ሳያድር ያየዋል።

መላው ህዝባችን በእልህና በቁጭት ላይ ያለህ ወገናችን ና የሀገራችን የነሰታነትና የዴሞክራሲ ሃይሎች በሙሉ፦ በአንዳርጋቸው ላይ ወያኔ የፈጸመው የአሸባሪዎች ውንብድና በየአንዳንዳችን ላይ የተፈጸመ በደል ግፍ ነው።

ይህንን የሽብርና የውንብድና ስርአት ለማስወገድ አብረን ከመነሳት ውጪ አማራጪ የለንም። የልዩነታችንን አጥር አፍርሰን የወየኔን እድሜ እንድናሳጥር ግንቦት 7 ለሁላችንም ጥሪውን ያቀርባል።

አንድ ሆነን የአንዳርጋቸውን ስምና ምግባር እንሁን!

አንዳርጋቸው የዘራው እና እየጎመራ ያለው የአርበኝነት ንቅናቄ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ወያኔ አንዳጋቸውን ያፈነበት ቀን የሚረግምበት ጊዜ ከዚህ በኋላ ሩቅ አይሆንም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ፋሽስታዊ ፕሮፖጋንዳው እና ምላሻችን !

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መንገድ ስንጓዝ ነው። ለዚህ የተዘጋጀ ሁሉ "አለሁ!" ይበል።

ማንም ዝርዝር መመሪያ በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን እንዲነገረው አይጠብቅ። የቆረጠና የመረረው ጀግኖች የሚገኙበት ድረስ ሄዶ ይቀላቀል። ከልቡ የቆረጠና ጥቂት ፍለጋ ያደረገ ሁሉ መንገዱን አያጣም።

1. ቀደም ሲል ንቅናቄዓችን - ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ - ያወጣውን የመጀመሪያ እርከን የትግል ጥሪ ተግባሪዊ ለማድረግ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በቁርጠኝነት በተግባራዊ ትግልቶች ይመንዘሩት፤
2. የተቆጣ፣ ጥቃት፤ ውርደት፤ ግፍ የመረረው ሁሉ፤ ለነፃነቱ ግድ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የስነ ልቦና ዝግጅት ያድርግ፤ ከወያኔ ሰላዮች ራሱን ተከላክሎ በያለበት በጥብቅ ከሚያምናቸው ጋር በመሆን በየአካባቢው በቡድን በቡድን ይደራጅ፤ በወያኔ ቀንደኛ ሹሞችና ወንጀለኞች ላይ ይሰልል፤ መረጃዎችን ለንቅናቄዓችን ይላክ።
3. በየአካባቢያችን የወያኔን ፋሽስቶችን የሚያሽማቅቁ፣ በሁለተናዊ መልኩ (በስነልቦና፤ ማኀበራዊ ተጽዕኖ በመፍጠር፣ በኢኮኖሚ) ጉልበታቸውን የሚቦረቡሩ፣ የሚያድከማቸው፣ ውስጣቸውን የሚሸረሽራቸው ሥራዎችን በቁጭትና በእልህ ሳናሰልስ ተግባራዊ እናድርግ።
4. በሕዝብ ጎራ ሳይሆን በጥቂቶቹ በወያኔ ፋሽስቶች ጎራ ፍርሃትና ብርክ የሚፈጥሩ የጀግንነት ሥራዎችን በቡድን በመደራጀት በመላው ዓለምና በኢትዮጵያ ውስጥ በብልሃት፣ በጥናትና በስልት በመተግበር ሕዝባዊ እምቢተኝነት እሁን እናድርግ።
5. ሁሉም ኢትዮጵያዊን የሚቻለውን ሁሉ ትንሿንም ጠጠር ብትሆን ወያኔና ጭፍሮቹ ላይ እንወርውር።

በደጀን የተሰለፈው ኃይል ደግሞ የዘማቹን ስንቅ በማዘጋጀት በገንዘቡ፤ በጉልበቱ፤ በመረጃ ይተባበር።

የአገር ማዳን የከተት ዘመቻ ላይ ነንና በእያንዳንዱ ጉዳይ ማብራሪያ እንዲሰጥ ሳንጠብቅ ቀበቶዓችንን አጠባብቀን እንነሳ። ድል እናደርጋለን! አገራችን ከዘረኞችና ፋሽስቶች መንጋጋ መንጭቀን እናወጣታለን!

**ድል ለኢትጵያ ሕዝብ!**
**ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ**

## <u>አዋጅ</u> አዋጅ !!!... ልብ ያለዉ ልብ ይበል ጆሮ ያለዉ ይስማ !!

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በቅድሚያ ኮሚንስቶች ላይ አነጣጠሩ

የዚያን ጊዜ ኮሚንስት ስላልነበርኩ ዝም አልኩ

ቀጥለው በሶሻሊስቶች ላይ አነጣጠሩ

የዚያን ጊዜ ሶሺያሊስት ስላልነበርኩ ዝም አልኩ

ለጥቀው ወደ ሰራተኛው ማህበር አነጣጠሩ

የዚያን ጊዜ የሰራተኛው ማህበር አባል ስላልነበርኩ ዝም አልኩ

በመጨረሻ ወደ እኔ መጡ በዚያን ጊዜ ለኔ የሚጮህልኝ አንድም ሰው አልተረፈም ነበር።

እስከመቼ ነው አንዳንችን ለአንዳችን እና ተባብረን እንዳንጮህ የዘር፣የእምነት እና የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት አሎሎ ትናጋችን ውስጥ ተቀርቅሮ በጩሀት እንኳን እንዳንደጋገፍ የሚያንቀን???? በ እውኑ ከላይ የተቀመጠው ትዝብት በትክክል ወቅታችንን አያንጸባርቅምን??!

ስለዚህ የአንዳርጋቸው መታገት እና ለወያኔ ተላልፎ መሰጠት የፈጠረው የአንድነት ስሜት በስርዓት ተኮትኩቶ በፍጥነት ፋፍቶ ወያኔን ወደመጣል እና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባት ዋና ዓላማችን ድረስ ሊወስደን ይገባል። ምንድን ነው የምንጠብቀው? እንዴትስ ነው በዚህ ደረጃ ያፍዝ ያደንግዝ የተደገሙብን?? ምን ዓይነት የመንፈስ ከሽፈት ነው እግር ከዎርች ያሰረን??

ምናልባት የምናሳድጋቸው ልጆች ይኖሩናል። አንዳርጋቸውም እኮ እንደሰው የወለዳቸው ህጻን ልጆች አሉት። አንድም ቀን አብሯቸው ውሎ አያቅም እንጅ። እዚህ በረሃ ውሃ እና ትርፍ ሰዓት ሲገኝ የታጋዩን ልብስ የሚችለውን ያህል ያጥብ ነበር፣ የልጆቹን ልብስ እንዳላጠበ ግን እርግጠኝ ሆኖ መናገር ይቻላል:: ከ ዓመት በላይ በረሃ ውስጥ ከረሃብ እና ጥም ጋር ሲታገል ልጆቼ የሚል ቃል ካፉ ወጥቶ አያቅም ። እንደሰው ልጆቹን ስለማይናፍቅ ግን አይደለም። ለዚች መከረኛ ሃገር ሙሉ ራሱን ስለሰጠ የልጅና የቤተሰብ ናፍቆት የመሰሉ ሰዋዊ ፈተናዎችን ታላቅ ራዕይን በሰነቀች ልቡ ውስጥ አስቀምጦት እንጅ። እና አንዳርጋቸው ልጆቹን ስለሚጠላ አይደለም የት እንደሚሄድ እንኳን ሳይነግራቸው ወደ በረሃ ሹልክ ያለው። ልጁን ማን ይጠላል!! የአንዳርጋቸው ጭንቀት ልጆቻችን ያለ ሃገር ወልደናቸው ምን ሊሆኑ ነው የሚል ነበርና ሃገር ሰርቶ፣ ማህበረሰብ ገንብቶ የማስረከብ ስራውን ቅድሚያ ሰጠው።

ምናልባት ሃብት፣ ትዳር ይኖረን ይሆናል። ግን ያለሃገር እና ያለነጻነት ሃብትና ትዳር ምንምን ይላል?? ይጣፍጣል?? አይመስለንም። በዘርህ እና በፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነትህ ምክንያት ከሞያሌ አሜሪካ፣ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

# እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ!

አንድን ሰዉ ጀግና የሚያሰኙ ብዙ መለኪያዎች አሉ፤ የእነዚህ መመዘኛዎች ስፋትና ጥልቀት ደግሞ እንደያገሩ ባህልና ወግ ይለያያል። የጀግንነት ትልቁ መለኪያ ጦር ሜዳ ዘምቶ ጠላትን ቁጭ ብድግ እያሰኙ መቅጣት ነዉ ብለዉ በሚያምኑ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አገሮች ዉስጥ “ ጀግንነት” የሚለዉን ጽንሰ ሀሳብ ጽንሰ ሀሳቡ በሚነካካዉ ሁሉም መልኩ መግለጽ አስቸጋሪ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ጽጌ ግን በዬትኛዉም አገርና ባህል አንድን ሰዉ ጀግና ሊያሰኙ የሚችሉ መስፈርቶችን በሙሉ ከወጣትነት ዘመኑ ጀምሮ ያሟላ ሙሉ ህይወቱን ለፍትህ፤ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ አሳልፎ የሰጠ ኢትዮጵያዊ ጀግና ነዉ። አገርህን አድን እያልንም ሆነ ወይም በርዕዮተአለም እየቀሰቀስን እልፍ አዕላፋትን ወደ ጦር ሜዳ ማዝመት ተችሏል፤ ለወደፊትም ይቻላል። ግን ይህ ስራ በራሱ ብዙም ጀግንነት የሚጠይቅ ስራ አይደለም። ለጦርነት ከቀሰቀስናቸዉ ሰዎች ጎን ተሰልፈን ጦር ሜዳ ድረስ መዝመት ግን እሱ አሱ ወደር የለሽ ጀግንነት ነዉ። አንዳርጋቸዉ ጽጌ የነጻነትና የፍትህ አርበኞችን ያፈራ ብቻ ሳይሆን እሱ እራሱ አንደ አንድ አርበኛ ዉግያዉ ወረዳ ድረስ ሄዶ አብሯቸዉ ሊዋደቅ የተዘጋጀ ቆራጥ ሰዉ ነዉ።

አንዳርጋቸዉ ፍትህ በሌለባቸዉ ቦታዎች መኖርን የሚጸየፍ ፍትህን የቀመሙትን ሰዎች ወይም ተቋሞች ደግሞ ባሉበት ቦታ ሁሉ በጽናት የሚታገል አሁንም የፍትህና የነጻነት ጠላቶች በመታገል ላይ እንዳለ በየመን ከሀዲዎች አዉሮፕላን ጣቢያ ዉስጥ ታግቶ ለወያኔ ዘረኞች ተላልፎ የተሰጠ ዘመን ስራዉን የማያደበዝዘዉ ጀግናና የኢትዮጵያ ህዝብ የቁርጥ ቀን ልጅ ነዉ።

አንዳርጋቸዉ ጽጌ ዕድሜዉ ከሃያ አመት በታች ከነበረበት ግዜ አንስቶ የፊዉዳሉን ስርዐት፤ የደርግን ስርዐት ዛሬ ደግሞ የዘረኞችን ስርዐት የተቃወመ ብቻ ሳይሆን የተፋለመ እዉነተኛ ጀግና ነዉ። አብረዉት ትግል የጀመሩ ግለሰቦች የራሳቸዉ ህይወት ከህዝብ አደራ በልጦባቸዉ ከትግል አለም ሲለዩ፤ አንዳንዶች በቃን ደከመን ብለዉ ወኔ ሲከዳቸዉ ፤ አንዳንዶች ደግሞ ለስልጣንና ግዜያዊ ጥቅም ሚኒልክ ቤ/መንግስትን ከተቆጣጠረ ሁሉ ጋር ቤተኛ ሲሆኑ አንዳርጋቸዉ ግን በአካሉም በመንፈሱም ያልተሸነፈ፤ ለገንዘብም ለስልጣንም ሲል ህሊናዉን ያልሸጠ ህዝብና አገር የሰጡትን የፍትህና የነጻነት አደራ እንደተሸከመ ከአርባ አመታት በላይ ጸንቶ የቆመ እዉነተኛ የነጻነት አርበኛ ነዉ። እንዳርጋቸዉ ጀግና ብቻ ሳይሆን በዘመናት ዉስጥ አንዴ ብቅ ብለዉ ሰማይን በብርሃን አድምቀዉ አንደሚሰወሩ ሰማያዊ አካላት ወይም ከዋክብት ለዚህ ዘመን ኢትዮጵያዉያን በድፍረት የነጻነት ችቦ የለኮሰ የህዝብ ባለአደራ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት የሆኑት የወያኔ ዘረኞችም ይህንን የህዝብ ልጅ አፍሪካ አዉሮፓና መካከለኛዉ ምስራቅ ዉስጥ በየሄደበት የተከታተሉትና በመጨረሻም እነሱን በመሳሰሉ ከሀዲ መንግስታት አማካይነት እንዲያዝ ያደረጉት አንዳርጋቸዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ የለኮሰዉ የፍትህና የነጻነት ችቦ እንደሚያጋልጣቸዉ ብቻ ሳይሆን ጠራርጎ እንደሚያጠፋቸዉም ስለሚያዉቁ ነዉ።

አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ “እባብን መመታት ጭንቅላቱን ነዉ” የሚባል የቆየ አባባል አለ። በእርግጥም እባብን ለመግደል ከጭንቅላቱ የበለጠ ጉዳት የሚያደርስበት ሌላ ቦታ የለም። ሆኖም እዚህ ላይ አንድ መርሳት የሌለብን ነገር አለ፤ እሱም እባብን ጭንቅላቱን መትተን ስንገድለዉ የሚሞተዉ አንድ እባብ ብቻ ነዉ፤ ብዙ እባቦች በህይወት ይኖራሉ፤ አዳደሶች ደግሞ ይወለዳሉ። ጅሎቹ የወያኔ ዘረኞች “እባብን መምታት” በሚለዉ ተረት ተሞኝተዉ አንዳርጋቸዉን ይዘዉ በማሰቃየት ወይም በመግደል ህዝባዊ ትግሉን አኮላሽተነዋል ብለዉ አስበዉ ከሆነ እጅግ በጣም ተሳስተዋል። የወያኔ ዘረኞች አንዳርጋቸዉን አሰሩ አላሰሩ የኢትዮጵያ ህዝብ እነሱን መታገሉን የሚያቆመዉ መብቱን፤ ነጻነቱንና የአገሩን አንድነት ለሱ ለራሱ ዉሳኔ ሲተዉለት ብቻ ነዉ። የሰዉ ልጅ እባብን መቀጥቀጡን የሚያቆመዉ እባብ መናደፉን ሲያቆም ብቻ ነዉ፤ የወያኔም ነገር እንደዚሁ ነዉ፤ ዘረኝነቱን፤ መብት ረጋጭነቱንና የአገር ድንበር መሸርሸሩን እስካላቆመ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ ይታገለዋል፤ መታገል ብቻ ሳይሆን የሚገባዉን ቅጣት ይሰጠዋል።

የወያኔ ዘረኞች እነሱ በእራሳቸዉ ሞክረዉ ሞክረዉ ያቃታቸዉን ነገር በዉንብድናና በክህደት እነሱን ከሚመስል የሌላ አገር መንግስት ጋር በመተባበር አንዳርጋቸዉ በህገወጥ መንገድ ታግቶ በህገወጥ መንገድ እጃቸዉ ዉስጥ እንዲገባ በማድረግ ለግዜዉም ቢሆን አንዳርጋቸዉን ከትግሉ ሜዳና ከትግል ጓደኞቹ ነጥለዉት ይሆናል፤ ሆኖም ግን የአንዳርጋቸዉ መታሰር በተሰማበት በአጭር ግዜ ዉስጥ ኢትዮጵያ ዉስጥና ከኢትዮጵያ ዉጭ እልፍ አዕላፋት ጀግኖች በቅጽበት ተፈጥረዉ አንዳርጋቸዉ ያበራዉን ችቦ አንግበዉ “እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ” እያሉ ትግሉን ተቀላቅለዋል።

ወያኔና የመን በመመሳጠር በጋራ አስረዉ የሚያሰቃዩት አንዳርጋቸዉ ጽጌ ሰነዓ ላይ ሲታሰርና ለወያኔ ተላልፎ ሲሰጥ አንድ ብቻዉን ነበር። ዛሬ ግን በየመኖች መታገቱና ለወያኔ ተላልፎ መሰጠቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ጆሮ በገባ ሳምንት በማይሞላዉ ግዜ አንድ ብቻዉን የታሰረዉ አንዳርጋቸዉ ጽጌ “እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ” ብለዉ እስከ መጨረሻዉ ወያንን ለመፋለም የቆረጡ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቆራጥ ኢትዮጵያዉያንን ከጎኑ ማሰለፍ ችሏል። ዛሬ ከዉጭዉ አለም ወደ ኢትዮጵያ የሚገባዉና ከኢትዮጵያ ወደ ዉጪዉ አለም የሚወጣዉ ድምጽ “እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ” የሚል የትግል ጥሪ ድምጽ ነዉ።

አንዳርጋቸዉን በህገወጥ መንገድ አግተዉ ለወያኔ ያስረከቡት የመኖችም ሆኑ ዘረኞቹ የወያኔ ባለስልጣኖች አንዳርጋቸዉ ዬት አንዳለ አናዉቅም ብለዉ አይክዱ ክህደት ክደዉ ነበር፤ ሆኖም አዉነትን ደብቀዉ ማቆየት እንደማይችሉ ስለተረዱ አንዳርጋቸዉን ለሁለት ሳምንታት ያክል ሲቀጠቅጡ ከቆዩ በኋላ ባለፈዉ ማክሰኞ አንዳርጋቸዉ እጃቸዉ ላይ እንደሚገኝ አምነዋል። በጥላቻ ተወልደዉ በጥላቻ ያደጉት የወያኔ መሪዎች አንዳርጋቸዉ ጽጌን የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አባል ስለሆነ ብቻ አይደለም እንደዚህ አክርረዉ የሚጠሉት። አንዳርጋቸዉ ለነጻነቱና ለእናት አገሩ ደር ድንበር መከበር አጥብቆ የሚሞግትና ሌሎችም እንደሱ ለነጻነታቸዉና ለአገራቸዉ አንድነት እንዲሟገቱ የሚገፋፋ የመብት፤ የነጻነትና የአገር አንድነት ጠበቃ ነዉ። ለዚህ ነዉ ይህንን የአገር አለኝታ የሆነ ሰዉ እስከ ግማሽ ቢሊዮን ዶላር ድረስ የሚሆን ገንዘብ ለየመኖች ሰጥተዉ ታግቶ እንዲሰጣቸዉ ያደረጉት።

የወያኔ ዘረኞች ይህንን አገርና የወገን አለኝታ የሆነ ሰዉ አስረዉ የሰዉ ልጅ አይቶትም ሰምቶትም የማያዉቀዉን ሰቆቃ ሁሉ እንደሚያወርዱበት ጥርጥር የለንም።አንዳርጋቸዉ ጽጌ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት፤ ነጻነትና የግዛት አንድነት መከበር ህይወቴ ታልፋለች ብሎ በአንድ ህይወቱ የተወራረደ ሰዉ ነዉ፡ እንደተናገረዉም ቃሉንም ያከበረ ሰዉ ነዉ። የወያኔ ዘረኞች ይህንን ጀግና ሰዉ ባሰቃዩና የስቃይ ድራማቸዉን በዚያ እንደ ቤት ዉስጥ ዕቃቸዉ በሚቆጣጠሩት ቴሌቪዥን ላይ ባሳዩን ቁጥር ማድረግ የሚገባን ነገር ቢኖር በቁጣና በእልህ ተነሳስተን “እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ” እያልን ትግሉን መቀላቀል ነዉ እንጂ አንገታችንን ደፍተን እነዚህ ዘረኞች እንድንሆንላቸዉ የሚፈልጉትን መሆን የለብንም።ህዝባዊ ትግሉ አምርሯል፤ ትንቅንቁ ተጀምሯል። ጎንበስ ቀና እያለ እንደ ህፃን ልጅ በእንብርክኩ ይዳዝ የነበረዉ የቱኒዝያ አብዮት በሁለት እግሩ ቆሞ እንዲሄድ መሐመድ ቦአዚዝ እራሱን መስዋዕት አድርጎ ማቅርብ ነበረበት። አይነካም አይሞከርም ሲባል የነበረዉን ሞባረክን በ15 ቀናት ከስልጣን አባርሮ ለፍርድ ያቀረበዉ የግብጹ አብዮት ከዳር ዳር እንዲቀጣጠል የሃያ ስምንት አመቱ ወጣት ከሊል መሐመድ ሰይድ መሞት ብቻ ሳይሆን አንደ ክትፎ መከታተፍ ነበረበት።

ኢትዮጵያን የሚጠብቅ አይተኛምና ለእኛም እንደ ሙሴ መርቶ ወደ ተስፋዉ አገር እንዲያደርሰን አንዳርጋቸዉ ጽጌን አድሎናል። አንዳርጋቸዉ ልክ እንደ ሙሴ የታገለለትን ማየት አይችል ይሆናል- እሱ የታገለለት አላማ ግን ምንም ጥርጥር የለንም ግቡን ይመታል። አንዳርጋቸዉ ከአርባ አመታት በላይ ለፍትህ፤ ለነጻነትና ለእኩልነት የታገለዉ አልበቃ ብሎት እራሱን መስዋዕት አድርጎ አቅርቦልናል፤ በዚህ ጀግና ሰዉ መስዋዕትነት የማይቀሰቀስና ትግሉን በቀጥታ የማይቀላቀል ኢትዮጵያዊ ካለ እሱ ከክብር ዉርደትን፤ ከነጻነት ዉርደትን የሚወድ ደሙ ከደማችን ያልተቀላቀለ ሰዉ መሆን አለበት። እኔ አንዳርጋቸዉ ነኝ የሚል ኢትዮጵያዊ፤ አገሩን ኢትዮጵያን የሚወድ ኢትዮጵያዊ፤ ጉልበትና አቅም ያለዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህንን አንዳርጋቸዉ የጀመረዉን ትገል ነገ ሳይሆን ዛሬዉኑ መቀላቀል አገራዊ ግዴታዉ ነዉ።

አንዳርጋቸዉ ጽጌ ወያኔን መቃወም ብቻ ሳይሆን ከመቃወም አልፎ የወያኔን ሰርዐት ለማሰወገድ ዱርቤቴ ብሎ በአይን የሚታይ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጀመረና የጀመረዉን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ወያኔን ፊት ለፊት ተፋልሞ ማስወገድ በሚችልበት አስተማማኝ ቦታ ላይ ያደረሰ ቆራጥና ደከመኝን የማያዉቅ ጀግና ነዉ።ለዚህ ነዉ የአንዳርጋቸዉ እንቅስቃሴ እንቅልፍ የነሳዉ ወያኔ በመንግስት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በመንግስታት ደረጃ ተመሳጥሮ ይህንን ጀግና ሰዉ በህገ ወጥ መንገድ በዉንብድና የያዘዉ። አንዳርጋቸዉ ጽጌ ደብዝዞ የነበረዉን ህዝባዊ ትግል ህይወት የዘራበት እሱ አራሱ ግን አንደ ሻማ የቀለጠ እኛ ኢትዮጵያዉያን እንደ ቱኒዝያዉ ቦዚአዚዝና እንደ ግብጹ ከሊድ ልንመለከተዉ የሚገባን የትግላችን አቀጣጣይ ችቦ የሆነ ሰዉ ነዉ። ዛሬ አንዳርጋቸዉ የሚፈልገዉና የሚመኘዉ በመታሰሩ ከንፈራችንን እየመጠጥን እንድንዘናጋና ሀሞታችን እንዲፈስ አይደለም። ይልቁንም የሱ ምኞትና ፍላጎት በሱ መታሰርና ስቃይ የእኛ ክንድ እንዲበረታና ሞራላችን እናሸንፋለን በሚል ጥርጥር የለሌለዉ ጽኑ ፍላጎት እንዲገነባ ነዉ።የአንዳርጋቸዉ ፍላጎት ቀፎዉ አንደተነካበት ንብ ‘ሆ’ ብለን ተነስተን እሱንና ሌሎች ተቆጥረዉ የማያልቁ ዜጎቻችንን የሚገድሉትንና እያሰሩ የሚያሰቃዩትን የወያኔ ዘረኞች ከአገራችን ምድር ጠራርገን እንድናጠፋ ነዉ።

አንዳርጋቸዉ እንደ ብዙዎቻችን አባት አለዉ፤ እናት አለዉ፤ ባለትዳርና የልጆች አባት ነዉ፤ ወንድም፤ እህትና ጓደኞችም አሉት። እሱ ግን ከእናቱ፤ ከአባቱ፤ ከልጆቹና ከትዳሩ አገሬ ኢትዮጵያ ትበልጥብኛለች ብሎ የአዉሮፓን ትኩስ ምግብና የተሞናሞነ ህይወት ምን ሊሆነኝ ብሎ ምግብና ዉሃ ብርቅ ወደ ሆነበት በረሃ ሄዶ ለኢትዮጵያ ዳግም ትንሳኤ ጠንካራ መሠረት ያኖረ ሰዉ ነዉ። አንዳርጋቸዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የጀግና ያለህ ብሎ ለግማሽ ምዕተ አመት አርግዞ በጣር የወለደዉ የቁርጥ ቀን ልጁ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ወያኔ ሃያ ሶስት አመት ሙሉ በዘር፤ በቋንቋ፤ በክልልና በሃይማኖት ሲከፋፍል የከረመዉን ህዝብ ካልሰበሰብኩ እንዳለ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌና በሌሎችም ፖለቲከኞች መታሰር ህዛባዊ ቁጣ ፈጠረ

የየመን መንግስት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ህገወጥ በሆነ መልኩ አሳልፈው ከሰጡዋቸው በሁዋላ ኢትዮጵያውያን አሁንም ቁጣቸውን እየገለጹ ሲሆን፣ አንዳንድ ወገኖች " የአቶ አንዳርጋቸው መታሰር ልብን የሚሰብር ቢሆንም፣ ወሳኙ ነገር ማዘን ሳይሆን ለለውጥ ቆርጦ በመነሳት መታገል ነው" ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የየመን መንግስት የወሰደውን እርምጃ እንዲሁም የኢህአዴግ መንግስት አቶ አንዳርጋቸውን አስሮ ማሰቃየቱን በመቃወም የሚያደርጉትን ተቃውሞ እንደቀጠሉ ነው። በአሁኑ ወቅት የጸጥታ ችግር በሚታይባት እስራኤል የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በቴላቪቭ ባደረጉት ተቃውሞ በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የተፈጸመውን ህገወጥ እርምጃ አውግዘዋል። ኢትዮጵያውያኑ እንግሊዝ በአቶ አንዳርጋቸው ጉዳይ ጣልቃ እንድትገባና የሚለቀቅበትን መንገድ እንድትፈልግም ጠይቀዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ መንግስት በሽብርተኝነት ሰበብ ያሰራቸውን በአገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉትን ፖለቲከኞች እንዲፈታ አንድነትና መኢአድ በጋራ እንዲሁም ሰማያዊ ፓርቲ ጠይቀዋል። አንድነት እና መኢአድ "ኢህአዴግ በምርጫ ዋዜማ የጀመረው እስር በአምባገነንነት መስመሩ ለመቀጠል የቆረጠ መሆኑን የሚያረጋገጥ ነው" በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ፣ " የሰሞኑ እስር እንደተለመደው የተቀነባበረ የስርዓቱ ድራማ ከመሆኑም በተጨማሪ የ2007ን ሀገራቀፍ ምርጫ በተለመደው ማሸማቀቅና ማወናበድ ለመውሰድ የተጀመረ የመጀመሪያ ርምጃ ነው ብለንም እናምናለን" ብሎአል።

ፓርቲዎቹ "የአንድነትና መኢአድ አባላትንና አመራሮቻችንን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በማሰቃየትና በማሸማቀቅ በመደብደብ የአካል ማጉደል ጉዳት በማድረስ የሚያደርገውን አስነዋሪ ተግባር አውግዘው፣ በግፍ የተታሰሩት አቶ ሀብታሙ አያሌው፤ አቶ ዳንኤል ሺበሺ፤ አቶ አብርሃ ደስታ እና አቶ የሺዋስ አሰፋ እንዲሁም በስርዓቱ በፖለቲካ አመለካከታቸውና እምነታቸው ብቻ ለእስር የተዳረጉ ፖለቲከኞች ፤ ጋዜጠኞችና ብሎገሮች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ" አሳስበዋል። ፓርቲዎቹ በተቃውሞ ጎራ የተሰለፉ ፓርቲዎች ይህን ህገ ወጥ እስር በማውገዝ እንዲሁም ኢፍትሀዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚደረገውን ሩጫ በመቃወም እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዲቆሙ" ጠይቀው፣ ይህንን ህገ-ወጥነት በህዝባዊና ሠላማዊ ንቅናቄ፣ በነፃና ፍትሓዊ ምርጫ መለወጥ እንዲቻል በጋራ እንዲሰሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት በበኩላቸው ገዢው ፓርቲ ስለምርጫ ሳይሆን አገርን ለማጥፋት እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ የት ነው ያለችው ሲሉ የጠየቁት ኢ/ር ይልቃል፣ ያመጸው ሁሉ ሽብረተኛ ሆኗል፣ በሰላማዊ ትግል የሚታገለውም፣ ጋዜጠኛውም ሽብርተኛ ሆኗል ያሉት ኢ/ር ይልቃል፣ አገሩን ማስተዳደሩ ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ፣ የትግሉ እንቅስቃሴ ከፍ ወዳለ ደረጃ መሸጋጋሩን ገልጸዋል።

## ሂውማን ራይትስ ወች አቶ አንዳርጋቸዉለወያኔ አገዛዝ መሰጠታቸዉን አወገዘ

ታዋቂው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ሂውማን ራይትስ ወች ባወጣው አስቸኳይ መግለጫ፣ አቶ አንዳርጋቸው ከማንም ጋር እንዳይገናኙ ተደርጎ ለኢህአዴግ የጸጥታ ሃይሎች ተላልፎ መሰጠቱን ከታማኝ ምንጭ ማግኘቱን ገልጿል። የየመን ባለስልጣናት ሰነዓ ከሚገኘው ኤል ራህባ አየር ማረፍያ ላይ እኤአ ጁን 23 ወይም 24 ከእንግሊዝ ኢምባሲ ጋር እንዳይገናኝ አድርገው አቶ አንዳርጋቸውን ወዲያውኑ ወደ ኢትዮጵያ ልከውታል ሲል ሂውማር ራይተስ ወች አስታውቋል። የአፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ሌስሊ ሌፍኮው የአቶ አንዳርጋቸው ደህንነት እንደሚያሰጋቸው ገልጸው፣ መንግስት ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጠበቆቻቸውና ከእንግሊዝ ኮንሱላር ሰራተኞች ጋር እንዲገናኙ እንዲፈቅድ ጠይቀዋል።

አለም በሙሉ የአቶ አንዳርጋቸውን ጉዳይ በአንክሮ እየተከታተለው መሆኑን የኢትዮጵያ ባለስልጣናት ልብ ሊሉት ይገባል ሲሉ ሌፍኮው ተናግረዋል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባወጣው መግለጫ ደግሞ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከየመን በሃይል ወደ ኢትዮጵያ እንዲወሰዱ መደረጋሸውን በአገሪቱ የሚገኙ የሰብአዊ መብት ድርጅቶችን ጠቅሶ ዘግቧል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች ከፍተኛ የሆነ ስቃይ እንደሚደርስባቸው የገለጠው አምነስቲ፣ በአቶ አንዳርጋቸውም ላይ ከፍተኛ ስቃይ ሊደርስበት ይችላል ሲል አክሏል።

## የግንቦት 7 ህዝቡን ለትግል የሚጋብዝ የክተት አዋጅ አወጀ

ድርጅቱ፣ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓም ባወጣው መግለጫ፣ "የየመን መንግሥት በህገወጥ መንገድ ያገተብንን የንቅናቀዓችንን አመራር በአስቸኳይ እንዲፈታ በተለያዩ መንገዶች ላለፈው አንድ ሣምንት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም" ብሎአል። "የአገሩን የረዥም ጊዜ ጥቅም ማየት የተሳነው የየመን መንግሥት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ አምባገኑን ወያኔ መርጦ መሪያችንን ለእርድ አሳልፎ ሰጥቶብናል፣ በዚህም ሳቢያ የየመን መንግሥት ይቅርታ የማያሰጥ፤ ዘመን የማይሽረው ታሪካዊ ስህተት ፈጽሟል" ሲል ግንቦት 7 አስታውቋል።" የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወዳጅ ጎረቤት ትሁትና ቀና ቢሆንም ጥቃት በሚያደርስበት የቅርብም ሆነ የሩቅ ጎረቤት ላይ ግን ቁጣውን የሚመጥን የአፀፋ እርምጃ መውሰድ ያውቅበታል።" በማለት የሚዘረዝረው የግንቦት 7 መግለጫ፣ "የወያኔ ፋሽስቶች አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በማሰቃየት ትግላችንን ማቀዝቀዝ እንደማይችሉ ልናረጋግጥላቸው እንወዳለን ።"ብሎአል።

"ወያኔ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በውንብድና ጠልፎ መውሰዱ የትግሉን ሜዳ አስፍቶታል ፤ የትግሉንም ዓይነት አብዝቶታል ። ይህ ደግሞ የወያኔ ፋሽስቶችን ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፍላቸዋል።" በማለት ድርጅቱ አጸፋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ አስታውቋል።የፓለቲካ ልዩነት አጥር ሆኖ ሳይከልላችሁ ከገናችን ለቆማችሁት የሲቪክ ማኅበራትና ዜጎች ሁሉ በወገናዊ ተግባራችሁ ልባችን ተነክቷ ልያለው ግንቦት 7፣ ከዚህ በላይ ደግሞ ለቀጣዩ ወሳኝ ፍልሚያም እንደምንቆም እና የወያኔን እድሜ እንደምናሳጥር እምነታችን አጠንክሮልናል" ሲል አክሎአል።መግለጫው ከዛሬ ጀምሮ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳርጋቸውጽጌን ሆኗል" ካለ በሁዋላ፣በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ ለደረሰውና ለሚደርሰው ጥቃት እያንዳንዱ የወያኔ ሹም በግል ዋጋ እንደሚከፍል ፣ ሕዝብ ለሚወስደው እርምጃ ተጠያቂው ራሱ ወያኔ መሆኑን እንዲሁም በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እስር የክተት አዋጅ መታወጁን በመጥቀስ" ህዝቡ ለጥሪው መልስ እንዲሰጥ ጠይቋል። አምነስቲ አያይዞም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከጎረቤት አገሮች የጸጥታ ሃይሎች ጋር በመተባበር በርካታ ኢትዮጵያውያን ያለፍላጎታቸው ወደ አገራቸው እንዲመለሱና ስቃይ እንዲደርስባቸው እየተደረገ መሆኑን ገልጿል። አምነስቲ የኢትዮጵያ ባለስልጣናት አቶ አንዳርጋቸው የታሰረበትን ቦታ እንዲያስታውቁ ጠይቋል

## ታዋቂዎቹ ፖለቲከኞች በማእከላዊ እስር ቤት መታሰራቸው ታወቀ

በፌደራል ፖሊሶች እየተደበደበ ወደ አልታወቀ ስፍራ ተወስዶ የነበረው ታዋቂው ፖለቲከኛና ጸሃፊ አብርሃ ደስታ ማእከላዊ እስር ቤት መታሰሩ ታውቋል። የአብረሃ መኖሪያ ቤት በፖሊሶች እንደተፈተሸም ለማወቅ ተችሎአል።

የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ወጣት ሃብታሙ አያሌው፣ የፓርቲው ምክትል የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ ዳንኤል ሸበሺ እንዲሁም የሰማያዊ ፓርቲ ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ አቶ የሸዋስ አሰፋ ዛሬ ፍርድ ቤት እንደሚቀርቡ ሲገለጽ፣ ዜናውን እስካቀረብንበት ጊዜ ስለተከፈተባቸው ክስ ለማወቅ የተደረገው ጥረት አልተሳካም። በኢትዮጵያ ሃሳባቸውን በነጻነት በመግለጻቸው እንዲሁም የተቃውሞ የፖለቲካ ድርጅቶችን በመቀላቀላቸው የሚታሰሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከመቼም ጊዜ በላይ ጨምሯል።

## ተቃዋሚ ፓርቲዎች የአንዳርጋቸዉን መታሰር አስመልክቶ የትገል አንድነታቸዉን በመግለጽ ላይ ናቸዉ

አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ በዉንብድና ተይዘዉ ለዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ተላልፈዉ መሰጠታቸዉን በመቃወም የተለያዩ አገር ዉስጥና አገር ዉጭ የሚገኙ የኢትዮጵያተቃዋሚ ድርጅቶች ተቃዉሟቸዉን በመግለጽ ላይ መሆናቸዉን የግንቦት ሰባት ህዝብ ግኙኝነት ክፍል አስታወቀ። ብዘዎቹ ፓርቲዎች ባወጡት ጋዜጣዊ መግለጫቸዉ የወየኔን መረን የለቀቀ ዉንብድናና ሽፍጥ አዉግዘዉ የትግል አንድነታቸዉን ገልጸዋል። ሁሉም ፓርቲዎቹ ያወጡትን መግለጫ እንዳላ ኢዚህ ማቅረቡ ባይቻልም የእንዳንዶቹ ፓርቲዎች ዋና ዋና ሀሳብ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ሰማያዊ ፓርቲ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሰብአዊ አያያዝ ያሳስበኛል አለ

የህወሓት/ኢህአዲግ አገዛዝ በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ዜጎችን በማፈንና በማሰቃየት ብሎም በመግደል የአፈና አገዛዙን ለረጅም ጊዜ ሲያራምድ መቆየቱ ዓለም የሚያውቀው ሀቅ ነው። በተለይም ባለፉት 10 ዓመታት የህዝብን ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለማፈን እስራትና ግድያውን ህጋዊ ለማስመሰል የተለያዩ አፋኝ አዋጆችን አውጥቷል። እነዚህን አዋጆችንም ተገን አድርጎ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችንና አባለትን፣ ጋዜጠኞችንና ጦማርያንን፣ እንዲሁም የእምነት ተቋማት መሪዎችን እና በአገዛዙ ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎችን ማሰሩን፣ ማሰቃየቱንና ግድያውን ተያይዞታል። በህገ መንግስቱ የተካተቱ የሰብዓዊ መብቶችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በሙሉ የሚጥሰውና የአምባገነንነት ስልጣኑን ለማራዘም ሲል ያፀደቀው የፀረ-ሽብር አዋጅ ከፀደቀበት እለት አንስቶ ኢህአዴግ ለስልጣኔ ያሰጉኛል የሚላቸውን ፍፁም ሰላማዊ ታጋዮችንና ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው በድፍረት የፃፉ ጋዜጠኞችን ብሎም የእምነት ነፃነታችን ይከበር ብለው የጠየቁ የሀይማኖት መሪዎችን በጠራራ ፀሃይ ያለምንም ወንጀል በዚሁ ህገ ወጥ አዋጅ «የፀረ ሽብር ግብረ ሀይል» በሚባል ማንነቱ በማይታወቅ የጨለማ ቡድን ወደ እስር ቤት እያጋዘ ይገኛል።

ይህን የሚያጋልጡ ሚዲያዎችንም ለማፈን እስር ቤቶችን ጨምሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር እያፈሰሰ የአየር ሞገድ ያውካል፤ በዚህ ሳያበቃ በሀገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙ ፖለቲከኞችን ለማሸማቀቅ እንደ ኢሳት ያሉ ሚዲያዎችን የአሸባሪ ልሳን ብሎ በመፈረጅ ሚዲያውን የሚጠቀሙትን ደግሞ ከአሸባሪዎች ጋር ንክኪ እንዳላቸው አድርጎ መወንጀሉን ቀጥሎበታል። እንደሰማያዊ እምነት ማንም አካል መልእክት የሚያስተላለፍበትን የሚዲያ ተቋም ሊመርጥለት እንደማይችል መንግስት እንዲገነዘበው ከዚህ በፊት በግልፅ ያሳወቀ ሲሆን አሁንም ፓርቲው በዚሁ የፀና አቋሙ እንደሚቀጥል በድጋሚ ይገልፃል።

ባጠቃለይ የዚህን ገዢ አካል የእውር ድንብር ሀገር የማስተዳደር ጉዞ ለመታገል በርካቶች በሰላማዊ መንገድ እየተንቀሳቀሱ ቢሆንም በህወሓት/ኢህአዲግ ግፍና መከራ ተገፍተው ስርዓቱን በሃይል እናስወግዳለን ብለው ሀገር ጥለው የተሰደዱ ዜጎችም እንዳሉ ይታወቃል። የህወሓት/ኢህአዲግ ማናለብኝነትና የስልጣን ጥመኝነትም በግለሰቦች ላይ ከሚያስከትለው ማህበራዊ ቀውስ በላይ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ አለመረጋጋትን አስከትሏል። በአሁኑ ሰዓትም ይህ ገዢ ፓርቲ የፈጠረው ስርዓት የሀገሪቷን ሰላማዊ የፖለቲካ ምህዳር በማጥበብ ሀገራችንን ወደ አልተፈለገ አለመረጋጋትና ቀውስ እየመራት ይገኛል። ፓርቲያችንም እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም በቅርቡ እየተፈፀሙ የሚገኙ ህገ ወጥ ድርጊቶች ስላሳሰበው ይህን መግለጫ ለማውጣት ተገዷል።

## ከትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ት.ህ.ዴ.ን) በየመን መንግስትና በወያኔ ስርአት ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ የተወሰደውን ያፈና በመቃወም የተሰጠ ድርጅታዊ

የወያኔ ኢህአዴግ ስርአት ባለፉት 23 ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል እየፈፀመ መቆየቱና አሁንም እየቀጠለበት መሆኑ ይታወቃል:: የወያኔ አምባገነን ስርአት ህዝቡን እየጨፈጨፈና ለነፃነት የቆሙትን ቁርጠኛ ታጋዮች በመግደል፣ የህዝቡን የትግል ማእበል መግታት እንደማይቻለው ካለፉት አባቶቹ መማር በተገባው ነበር::

ትናንት በወያኔዎች ቀጥተኛ መሪነት ይካሄድ በነበረው የትጥቅ ትግል በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ጀግኖች ለጭቁኑ ህዝብ ሲሉ ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ተዋግተው በከፈሉት መስዋእትነት ህዝባዊ ትግሉ በበለጠ እልህና ቆራጥነት ሲቀጥል እንጂ፣ በመስዋዕትነቱ ምሬት ተደናግጦና ተስፋ ቆርጦ ትግሉ ወደ ኋላ ሲመለስና ትርጉም የለሽ ሲሆን አልታየም፡፡ ምክንያቱም ትግል ሲባል ሁሉም አይነት መስዋእትነት ከፍለህ ከአፈናና ከጭቆና ነፃ በማውጣት ለህዝቡ ፍትህ፤ እኩልነትና ዴሞክራሲ ማስፈን ስለሆነ፡ ይህ በታጋይ እንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የተፈጸመው የእገታ እርምጃ ትግሉን የበለጠ ያቀጣጥለዋል እንጂ ወያኔ እንደተመኘው ትግሉን አያዳክመውም:: አንዳርጋቸው እንደ አንድ ታጋይ መሪ ለትግሉ የከፈለው መስዋዕትነትም ለዘአለም ህያው ሆኖ ይኖራል።

ስለሆነም የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ት.ህ.ዴን/ ይህ በየመን መንግስት በታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የተፈፀመው ታሪካዊ ስህተት በሁሉም የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ላይ የተፈፀመ እንደሆነ በማመን እኩይ ተግባሩን በፅኑ ያወግዛል ። ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌ ለህዝብ ብሎ የከፈለው መስዋእትነት አላማውን አምነው ለህዝብና ለሃገር ነጻነት ትግሉ የሚያስፈልገውን የህይወት መስዋእትነት ሁሉ ከፍለው አገራቸውን ነጻ ለማውጣት የቆረጡ እልፍ አእላፍ ጀግኖችን ይፈጥራል ብሎ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ትህዴን ያምናል። በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ አንዳርጋቸው ፅጌና ሌሎች በሺህ የሚቆጠሩ ታጋዮች እስከዛሬ ዋጋ የከፈሉለትን ትግል ለድል ለማብቃትና የአምባገነኑ ስርአት እድሜ ለማሳጠር ዛሬውኑ ትግሉን እንዲቀላቀል በዚህ አጋጣሚ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ት.ህ.ዴ.ን / ጥሪውን ያቀርባል።

ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲና በአቶ አባንግ ሜቶ የሚመራዉ የሶሊዳርቲ ንቅናቄም የአቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌን መታፈንና ለወያኔ ተላልፎ መሰጠት አስመልክቶ ጠንከር ያለ መግለጫ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አዉጥተዋል።

## አዋጅ አዋጅ !!!........... . . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

ከጎንደር አውስትራሊያ፣ ከጋምቤላ ካናዳ ድረስ በምትሳደድበት እና በምትታደንበት ሁኔታና ዘመን ውስጥ እስከ አፍንጫ ተነክሮ ሃብትና ትዳር ምንድን ናቸው?? ምናልባት እንደቀንድ አውጣ ራሳችንን የምንቀብርባቸው ቅርፊቶች ካልሆኑ በስተቀር። አንዳርጋቸው ለዚች ጣጣዋ ያላላቀ ሃገር፣ለዚች የምትንገላታ ባንዴራ ኪሱ ውስጥ 5 የአሜሪካን ዶላር እስኪቀረውና አላላውስ እስኪለው ኢትዮጵያዊ እምነቱን ለመግለጽ፣ለማስተማር፣ ለመቀስቀስ ዞሯል ወጥቶ ወርዷል።

ምናልባት - - - - እያልን ብዙ እንደምክንያት የሚጠቀሱ ነገሮችን ስንደረድር ልንውል እንችላለን። አንድን ሃገር እና ትውልድ ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋ እየጣረ ያለ ስርዓትን በግልጽ እስከ ህይወት መስዋዕትነት ላለመታገል ብዙ ምክንያት እያነሳን ራሳችን ልንሸነግል እንችላለን። ከቁም ሞት እያዳነን አይደለም እንጅ!!

ከቶ በምን ዓይነት ተፈጥሯዊ ወይ ሰው ሰራሽ ተጠየቅ ይሆን አንድ የሽፍታ ቡድን 97 ሚሊዮን ህዝብ ለ 23 ዓመታት አምበርክኮ ለገዛ የሚሞክረው?? ለቆመ አይደለም ለሞተ የሚገርም ጉድ አይደለምን?? ከዚህ በላይ አሳፋሪ ነገርስ በየትኛው የዓለም ጫፍ ቢታሰስ ይገኛል??? ይህ አዋጅ ለተደራጁ የፖለቲካ ሃይሎች ብቻ አይደለም፣ ለሲቪክ ተቋማት ብቻ አይደለም፣ ለወጣቱ ሃይል ብቻ አይደለም፣ ለወንዶች ብቻም አይደለም። ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የታወጀ አዋጅነው። ተነስ!!! መሳሪያ አንሳ!!! ወያኔን በጉልበትህ ከራስህ ላይ አውርድ!!! የመከራ እና የውርደት ዘመን ይብቃ!!! ያለበለዚያ ሁለት ምርጫዎች እጃችን ላይ አሉ፡- አንድ በጋራ ታግለን ነጻነታችን ማዎጅ ሁለት ባርነትን መርጦ ፣ባርነትን ተቀብሎ እንደባሪያ መገዛት!! በቃ !!

አንድ አለመሆናችንን የታዘቡ እናም የናቁን፣ በየስርቻው መወሸቃችንን የተገነዘቡ እናም የተጸየፉን የተጻፈ እና ያልተጻፈ የረጅም ጊዜ ፖሊሲ ያላቸው የብሄራዊ ቤተሰብ ምስረታ ሂደታችን አደናቃፊ ብሄራዊ ጠላቶቻችን ነጻነታችንን ስለማይፈልጉ ቅኝ ገዝዎቻችን ሌት ተቀን እየተባበሯቸው ነው። የሚፈልጉትን ሰው አንስተው እየሰጧቸው ነው።

እልፍ አዕላፍ ኢትዮዮጵያዊያን ከተጠጉበት እየታደኑ ለእርድ ሲቀርቡ ይህው ድፍን 23 ዓመት ሞላን። አንዱ ከሆነ ሃገር ሲያዝ እና ተላልፎ ሲሰጥ እንደነጩ በሬ የጓዳ አጋራችን ደም አልከረፋ ሲለን፣ እኔ ምን አገባኝን ስንቀኝ፣ይህ እኮ የኮሚኒስቶች ጉዳይነው፣ የነከበደ ጣጣ ነው እዛው ይወጡት ስንል በየተራ እየተለቀምን እያለቅን ነው።

አንዳርጋቸው ለዕርድ ቀርቧል!! ምናልባት ታሪካዊ ጠላቶቻችን የእርድ ቢላዎቻቸውን ስለው ደም በቋጠረ የበቀል አይን ከበው እያዩት ይሆናል። ሊያርዱት!! እንደታሳሪ ፈርቶ ሳይሆን መልካም ስራ ሰርቶ ክርስቶስ/አላህ ዙፋን ፊት እንደቀረበ ጻድቅ በኩራት ቆሞ አንገቱን እንደሚሰጥ ግን ጥርጥር የለንም። ታዲያ የኛ አዋጅ አንኳር መልዕክትም ያለው እዚህ ጋር ነው። አንዳርጋቸው በየሰርጡ እና በየእርሻው እየዘረ የዘራው የአንድነት፣ የኢትዮጵያዊነት፣ የነጻነት፣ የፍትህ ፣የዴሞክራሲ ዘር የሱ በድን ላይ ይብቀል፣ ደሙን ጠጥቶ ይፋፋ ከሱ በኋላ ግን ይብቃ የሚል ነው። ኢትዮጵያዊዩ አንድ ሆኖ ተቆጥቶ እንደ አንበሳ ያገሳ ዕለት የሰሜን ነፋስ እንደነካው ጉም በነው እንደሚጠፉ እናውቃለን። ያውቃሉ። ማድረግ ያቃተን ተደጋግፈን መቆም፣ እጅለ እጅ መያያዝ፣ አንድ ላይ መጮህ አንድ ላይ የቁጣ ክንዳችን መሰንዘር ብቻ ነው። ታዲያ ካሁን በኋላ የአንዳርጋቸውን አንገት የቆረጠ ካራ ለሌሎች ተረኞችም ተስሎ እንዲቀመጥ እንፈልጋለን?? የማንፈልግ ከሆነ እጆቻችንን እርስ በርስ አጣምረን መብረቅ እናስተፋቸው፣ ነጎድጓድ እንሙላቸው። ከዚያ ውጤቱን በታሪክ ገጽ ላይ ጎልቶ ተጽፎ እናየዋለን። ያለበለዚያ ኢትዮጵያዊያን የለንም ጨርሰን ጠፍተናል ማለትነው። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ አዋጅ አዋጅ፣ ልብ ያለው ልብ ይበል፣ ጆሮ ያለው ይስማ !!!ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት ሳትጠፋ ጠላቶችህን አጥፋ !!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## እኔም አንዳርጋቸዉ ነኝ! . . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

እንደ ወጣ የቀረ ጀግናችን ነዉ፡፡ አዎ አንዳርጋቸዉ እንደ ስሙ አንድ ሊያደርገን ጎንበስ ቀና ሲል የለየላቸዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች እጅ ወድቋል። አንዳርጋቸዉን የምንወድና የአንዳርጋቸዉ በድንገት ከትግል ሜዳ መለየት ያንገበገበን በብዙ ሚሊዮኖች የምንቆጠር ኢትዮጵያዉያን ወደድንም ጠላን ዛሬ ያለን ምርጫ ከወያኔ ጋር ተናንቀን እኛንም አገራችንንም ነጻ ማዉጣት ወይም በወያኔ እየተረገጥን ልጆቻችንን፤ ጓደኞቻችንንና ወዳጅ ዘመዶቻችንን ተራ በተራ እየገበርን መኖር ብቻ ነዉ። አንዳርጋቸዉ ዛሬ እጁ በዘረኞች ተይዞ የሚሰቃየዉ ከባርነት ነጻነት፤ በግሉ ከሚያገኘዉ ህብትና ብልጽግና የአገሩ ህልዉና በልጦበት ነዉ። አንዳርጋቸዉንና አገሬን የምንል ኢትዮጵያዉያን ከዛሬ በኋላ ይህ አንዳርጋቸዉ ያቀጣጠለዉ ህዝባዊ ትግል ወያኔንና ወያኔ የገነባዉን ዘረኛ ስርዐት እስካልደመሰሰ ድረስ ለአንድም ቀን ቢሆን እንቅልፍ ሊወስደን አይገባም። አንዳርጋቸዉ የሂሊናም ሆነ የአካል እረፍት አግኝቶ እፎይ የሚለዉ እሱ ከወያኔ ቁጥጥር ስር ነጻ ሲወጣ አይደለም። አንዳርጋቸዉ እፎይ ብሎ የሰላም እንቅልፍ የሚተኛዉ እሱ የጀመረዉን የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ጉዞ እኛ ስንጨርስለት ብቻ ነዉ። ስለዚህ ጉልበት ያለህ በጉልበትህ፤ ገንዘብ ያለህ በገንዘብህ፤ እዉቀት ያለህ ደግሞ በእዉቀትህ ነገ ዛሬ ሳትል ይህንን ትግል ተቀላቀል።